በ: אורית רז
ምሳሌዎች: שחר קובר
הוֹצָאָה: מודן
የእድሜ ክልል: ታዳጊዎች

קְרִיאָה

አብሮ ማንበብ

ታሪኩን በማንበብ በንቃት እንዲቀላቀሉ ታዳጊዎቹን ማበረታታት ይችላሉ። እነርሱ የግጥም ቃላትን ማጠናቀቅ፣ በፊት ገጽታ እና በትክክለኛ የእጅ ምልክቶች በእንስሳት መካከል የሚደረገውን ውይይት ማጀብ እና በታሪኩ ውስጥ የሚታዩ የእንስሳትን ድምጽ መፍጠር ይችላሉ።

שִׂיחָה

ሰንበትን ወደ መቀበል

ታዳጊዎችን መጠየቅ ይችላሉ፡- በሰንበት ምን ማድረግ ይወዳሉ? ቤተሰቡ ለሰንበት ልዩ ዝግጅቶች ካላቸው፣ እነርሱን ለልጁ መንገር እና ማጋራት ጠቃሚ ነው

חֵקֶר

?እንስሳቶቹ የት አሉ

መጽሐፉ ንብ፣ ኤሊ፣ ጉንዳን፣ ዶሮ፣ ላም እና ጥንቸል በተለይ ይገልፃል። በመፅሃፉ ውስጥ ባሉት ስዕላዊ ማብራሪያዎች ውስጥ ታዳጊዎች የተለያዩ እንስሳትን እንዲለዩ ጠይቋቸው እናም እያንዳንዱን እንስሳ በልዩ ድምፅ አጅበው ወይም ሌላ የባህሪይ ዝርዝሮችን ይጨምሩበት፡- ንቧ ዝምምም ትላለች፣ ጥንቸሉ ይፈናጠራል፣ ኤሊ በዝግታ ትሳባለች፣ እና ላሟ ትጮኻለች።

הַמְחָשָׁה

!እናም አሁን - ኤሊ

በእጅዎ መዳፍ ኤሊ እንዴት ይሰራል? መዳፉን በቡጢ ይዝጉና በውስጡ አውራ ጣትን ይደብቁ። ኤሊውን ወደ ውጪ ይጥሩ፣ አውራ ጣትን አውጥተው ሰላም በማለትያንቀሳቅሱት። እቤት ውስጥ ከሚገኙ በሁሉም መዳፎች ብዙ ዔሊዎችን መፍጠር ትችላላችሁ እራስዎ ኤሊ መሆን እና በአራት እግሮች ላይ በዝግታ መሄድ ይችላሉ። ደክሞታል ወይ? በ"ቤትዎ" ውስጥ ለማረፍ ወደ ውስጥ ይግቡ።

סִרְטוֹנִים

Pinterest

Pinterest – **የእደ-ጥበቦች፣ መዝሙሮች እና ሌሎች ተግባራት "ሰንበት በጫካ ውስጥ በሚለው መጽሐፍ ገጽ ላይ በሲፍሪያት ፒጃማ ውስጥ በ** Pinterest **ላይ።**

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org